# <u>ፎቶና ታሪኩ - እስረኞች</u>

*መስፍን ማሞ ተሰማ*

*{ፈላስፋ በወህኒ ቤት በራፍ ላይ እንዲህ የሚል ፅሁፍ አነበብኩ አለ፤ ይህች ቦታ የመከራና የጭንቅ ናት፤ ያልሞቱ (በሕይወት ያሉ) ሰዎች የሚቀበሩባት መቃብርም ናት። የወዳጆች መፈተኛ፤ የጠላቶች መደሰቻ የሆነች ቦታ ናትና።} አንጋረ ፈላስፋ (የፈላስፎች አነጋገር) ፤ በሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ በ1953 ዓ/ም ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተተረጎመ።*


*****************************************************************

*በወያኔ አገዛዝ፤ በወያኔ ቀንበር*
*የካቴናው ስርስር የኮረንቲው ንዝር*
*የመቀመቅ ፍዳው የጨለማው እስር*
*የሰቆቃው ንረት የአውሬዎቹ ምንዝር*
*እንዴት እንደ ሆነ እንዴት እንደነበር*
*ፍትህ በሌለበት ለዳኛ ከመንገር*
*ጠበቃ ከማቆም ዕማኝ ከመደርደር*
*ይኸው የኛ ፎቶ ታሪኩን ይናገር።*




***<u>ፎቶ፤</u>*** *ሴፕቴምበር* 14 2011 (*እአአ*) *የወያኔ ፀጥታ ሀይሎች አዲስ አበባ ላይ አንዱዓለም አራጌን በቁጥጥር ስር ሲያውሉ። እነሆ ከዚህ ቀን ጀምሮ ወጣቱ ትንታግ የሠላማዊ ትግል አራማጅ ፖለቲከኛ በወህኒ ቤት ይገኛል። ህግና ዳኛ ወያኔንና አገዛዙን ለመጠበቅ በቆሙባት ኢትዮጵያ ለህዝብ መብት፤ ነፃነት ፍትህና እኩልነት ተሟጋቹ አንዱዓለም አራጌ በሽብርተኝነት ህገ መንግሥቱን በሀይል ለመናድ በሚል በተመሰረተበት ክስ ዕድሜ ልክ እስራት ተፈርዶበት በር ተዘግቶበታል። ዘረኞችና ዘራፊዎች 'መንግሥት' በሆኑባት ኢትዮጵያ ኢትዮጵያዊነትና ፍትህ ጠያቂነት 'ሽብርተኝነት' ሆኗል። ዳኞች እነሱ አቃቤ ህግ እነሱ ህጉም ለእነርሱ። እነሆ በ*2002 *ዓ/ም* (2010) *ምርጫ ወቅት በህወሃት/ኢህአዴግ ገዢ ፓርቲ እና በተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን በተካሄደው ውይይት አንዱዓለም አራጌ 'መድረክ'ን ወክሎ እንዲህ አለ፤ "ኢህአዴግ አንድም ቀን ስሜታዊ እንጂ ምክንያታዊ ውይይት አድርጎ አያውቅም። በመሰረቱ ኢህአዴግ አምባገነናዊ መንግሥት ነው። በግልፅ መነጋገር አለብን። የአምባገነንነቱ መሰረት ደግሞ ፍርሃት ነው። በሀገራችን 'የፈሪ ዱላው አስራ ሁለት ነው' ይባላል። ኢህአዴግ ፈሪ ስለሆነ የተለያዩ የፍርሃት ህጎችን እያወጣ የኢትዮጵያን ህዝብ ቀይዶ፤ ጫንቃው ላይ ተጭኖ ለመግዛት እየሞከረ ነው ያለው። ለምሳሌ በደርግ ጊዜ አንድ አዋጅ ወጥቶ ነበር፤ አዋጅ* 767 *የሚባል። ያነበበ ያስነበበ አሽሙር የተናገረ* 15 *ዓመት ይፈረድበታል ይላል። ዛሬ ኢህአዴግ የሚያወጣው የፀረ ሽብር ህግ ፤ የፓርቲዎች ሥነ ምግባር አዋጅ የኢትዮጵያን ህዝብ ለጉሞ እንዳይንቀሳቀስ የሚያደርግ ህግ ነው። ኢህአዴግ ከ'*97 *ዓመተ ምህረት በሁዋላ የተማርኩት ነገር አለ ይላል። የተማረው አንድ ነገር ነው። በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ የኢትዮጵያ ህዝብ ኢህአዴግን እንደማይመርጠው ያውቃል። ጠንቅቆ ያውቃል። ስለዚህ ሜዳውን ሁሉ ዘጋግቶ ለብቻው መሮጥ ይፈልጋል። ምንድን*

ነው እያለ ያለው? ተቃዋሚዎች እግር እስኪያወጡ እጠብቃለሁ፤ እግር ሲያወጡ እቆርጣለሁ ነው። ይሄ ነው የኢህአዴግ ዴሞክራሲያዊነት። የሚዲያ ተቋማትን እንይ። በ1987 ዓ/ም ኢትዮጵያ ውስጥ 367 ነፃ ጋዜጦች ነበሩ። ዛሬ አስር እንኳን በቅጡ ተቆጥረው አይሆኑም። ሌላ የብርቱካን ሚዴቅሳ ጉዳይ ተነስቷል። ብርቱካን ወንጀል የለባትም። ወንጀል እንደማትሰራ ፍትህን




ጠንቅቃ የምታውቅ በፍትህ አደባባይ ፍትህን ለህዝብ መስጠት የምትችል ዳኛ እንደ ሆነች ኢህአዴግ ያውቃል። ግን ብርቱካንን ልዩ የሚያደርጋት ምንድን ነው? ብርቱካን አንገቷን ቀና አድርጋ የምትሄድ የኢትዮጵያ ሴቶችን ለኢትዮጵያ ህዝብ ምሳሌ የምትሆን ዳኛ፤ የፖለቲካ መሪ መሆኗን ያውቃል። እንዲህ አይነት ግለሰብ በኢትዮጵያ ምድር እንዲፈጠር ኢህአዴግ አይፈልግም። ስለዚህ አንገቱን ማስደፋት ይፈልጋል። ሌላ - የህግ የበላይነት ተደጋግሞ ይነሳል። ከ1993 ዓ/ም በሁዋላ በኢትዮጵያ የህግ የበላይነት የሚባል ነገር ቀርቷል። ጭላንጭሉም ተዳፍኗል። ከ'93 ዓ/ም በሁዋላ አንድና አንድ ሉዐላዊ ግለሰብ አሉ፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ብቻ ናቸው። በፊት የፓርቲ አምባገነንነት ነበር። ዛሬ የግለሰብ አምባገነንነት ነው ያለው። ሌሎቹ የኢህአዴግ ሊቃነ መናብርቶች ወይም ሹማምንቶች የጠቅላይ ሚኒስትሩን ዙፋን ከመሸከም ያለፈ ሃላፊነት የላቸውም። የተናገሩትን መልሰው ማስተጋባት ነው። የህገ መንግሥቱ አንቀፅ 30 ምን ይላል? ማንም ሰው የሌላውን ህዝብ መብት እስካልጎዳ ድረስ በነፃ የመሰብሰብ የመሰለፍ መብት አለው ይላል። የታለ ያ መብት የሚከበረው? በተለይ ከ'97 ዓ/ም ምርጫ በሁዋላ። ንገሩና! አዲስ አበባ ውስጥ ስንት ጊዜ ነው ሰልፍ ጠይቀን የተከለከልነው? የኢትዮጵያ ህግ እንደውም ህገ መንግሥቱ ማፌዣ ሆኗል። ኢህአዴግ ከራሱ ፕሮግራም የቀዳውን ህገ መንግሥት በመጣስ የመጀመሪያውም የመጨረሻውም ኢህአዴግ ነው። ሌላ አንድ ነገር ልጥቀስ - በዚህ አገር የህግ የበላይነት እንደሌለ።

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለ ሥልጣን ሠራተኞች አስተዳደር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ተብሎ የወጣ አለ። በዚህ ደንብ መሰረት በሌላ ሁኔታ የተደነገገ ቢኖርም ዋና ዳይሬክተሩ በሙስና የተጠረጠረን እምነት ያጣበትን ማንኛውንም መደበኛውን የዲሲፕሊን አፈፃፀም ሥርዐት ሳይከተል ከሥራ ማሰናበት ይችላል - ይላል። እንዲሁም በንዑሰ አንቀፀ 2 በዚህ አንቀፀ ንዑስ 1 መሰረት ከሥራ የተሰናበተ




ሠራተኛ በየትኛውም የፍርድ አካል ውሳኔ ወደ ሥራ ለመመለስ መብት የለውም - ይላል። ይህ ምን ማለት ነው? ዳይሬክተሩ በፈለገ ጊዜ ሰውን ማባረር ይችላል። የዐይኑ ቀለም ባላማረው ጊዜ ሊያሰናብተው ይችላል። የሚገርመው ነገር ግን ይህ ሰው በምንም ዐይነት መልኩ ወደ ሥራ ሊመለስ አይችልም። የህገ መንግሥቱ አንቀፅ 25 ምንድን ነው የሚለው? የሰዎች በህግ ፊት እኩልነት - የታለ እዚህጋ? ንገሩና! አንድ ሰው የመሰለውን የሚወስንበት ነው። ይሄ እናንተ ያወጣችሁት ህግ ነው። የናንተ ሚኒስትሮች ተሰብስባችሁ የሰራችሁት ነው። አረጋዊ ገብረ ዮሀንስ ምንድን ነው የሆነው በዚህ ሰሞን በምርጫ? አገር አለኝ ፍትህ አለ ሠላም አለ ብሎ በሚኖርበት ነው በእናንተ ሰዎች ተወጋግቶ የተገደለው። ስለ ነፃ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ ታወራላችሁ። ንገሩና የታለ?! ይኸው መርሳ ላይ ከሁለት ቀን በፊት 14 አባሎቻችን በፌዴራል ፖሊስ ሲደበደቡ አድረው አልተለቀቁም? ፌዴራል

ፖሊስ የማን ነው? የናንተ ነዋ! እንወዳደር ምርጫው ፍትሃዊ ነው በሚዲያ ታደነቁሩናላችሁ። የታላችሁ ታዲያ? ሌላ ምሳሌ እንውሰድ፤ የፀረ ሙስና ኮሚሽን። የራሱ ፖሊስ አለው፤ የራሱ መርማሪ አለው፤ ራሱ ከሳሽ ነው። ይሄ ብቻ አይደለም፤ የጉምሩክ ባለ ሥልጣን - የራሱ ፖሊስ አለው፤ ራሱ መርማሪ አለው፤ ራሱ ከሳሽ ነው። ምን ዐይነት ዴሚክራሲ ነው? ምን ዐይት የህግ የበላይነት ነው? ሌላ ተደጋግሞ የተነሳ ነገር አለ። ተደጋግሞ የተነሳው ነገር የብሄር ብሄረሰቦች መብት ተከብሯል ትሉናላችሁ። አንድ የኦሮምኛ ተናጋሪ ፕሬዚዳንት ስለ መረጣችሁ የኦሮሞ ህዝብ መብት ተከበረ ማለት አይደለም፤ እቅጩን ልንገራችሁ። አማርኛ ተናጋሪ የአማራ ክልልን ህዝብ ስለመራ መብቱ ተከበረ ማለት አይደለም። የኢትዮጵያ ህዝብማ መብቱ ተረግጧል፤ ታውቂታላችሁ። ጥያቄው ዛሬ እናንተ መመለስ ያለባችሁ - መቼ ነው ይህንን ኢፍትሃዊነታችሁን የምታቆሙት? መቼ ነው ቶርቸር የምታቆሙት? መቼ ነው ማሰቃየት የምታቆሙት? መቼ ነው ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ የምትወርዱት? ይህን ጥያቄ መልሱልን ዛሬ፤ መልሱ!"

ታላቁ የኢትዮጵያ ልጅ ወጣቱ ፖለቲከኛ አንዱዓለም አራጌ ይህንን አስደናቂ ንግግር ካደረገና 'መቼ ነው ከኢትዮጵያ ህዝብ ጫንቃ የምትወርዱት?' ብሎ ከጠየቀ እነሆ ይህ ጥንቅር ለንባብ ሲበቃ (2010 ዓ/ም) ስምንት ዓመት አልፎታል። መሰሪው መለስ ዜናዊ የአንድነት ለፍትህና ዴሞክራሲ ፓርቲ (አንድነት) ምክትል ሊቀመንበር አንዱዓለም አራጌ



ይህንን ሲናገር አራት ኪሎ ቤተ መንግሥት መሽጎ እያዳመጠ ነበር። ዘረኛውና በቀለኛው የህወሃት አርኪቴክት መለስ ዜናዊ አንዱዓለምን በ'ሽብርተኝነት' ወንጅሎ/አስወንጅሎ የዕድሜ ልክ እስራትም አስበይኖበት በጥቂት ወራት ከሚያፌቅረው የምኒልክ ቤተ መንግሥትና የኢትዮጵያ መንበር ላይ በሀሰተኛው መስቀላቸው ሲባርኩት የኖሩትን ነፍስ አባቱን አቡነ ጳውሎስን አስከትሎ ተሰናበተ። የግፍ ፅዋው ሞልቶ ይዞት ሄደ። እርሱ ቢያልፍም ዘግናኙ ሌጋሲው የህወሃት ናዚስታዊ የዘረኝነት ግፍ ግድያ ቶርቸርና እስር ዛሬም እጅግ በሰፋና በከፋ መልኩ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ተጠናክሮ ቀጥሏል። (ፎቶ፤ እስካፍንጫው የታጠቀው የናዚስቶቹ ጦር በኦሮሞና አማራ ክልሎች በተነሳው ህዝባዊ ተቃውሞ ወቅት አቅም አልባዎችን ሲያሰቃይ - ሶሻል ሚዲያ)



ለኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነትና መብት ራሱን አሳልፎ የሰጠው ወጣቱ የሠላማዊ ትግል አራማጅ ፖለቲከኛ የሁለት እንቦቃቅላ ልጆች አባት ሆኖ እያለ እነሆ ልጆቹንና ውድ ባለቤቱን ባዶ ቤት ጥሎ እርሱ ለሀገሩና ለህዝቡ ወህኒ ቤት ተዘግቶበት ይኖራል። ናዚስቶቹ አንዱዓለምን በአካለ ሥጋ አሰሩት እንጂ ፅኑ መንፈሱንና አይበገሬ ኢትዮጵያዊነቱን፤ ስለ ኢትዮጵያ መፃዒ ዘመን ተስፈኝነቱንና ስለ ህዝቡም ልዕልና ክብር ሠላምና ዴሞክራሲ ያለውን የተስፋ ፅናትና የትግል መንፈስ ከቶም

ሊያስሩት አይችሉም፤ አልቻሉምም። በእስር ህይወቱ ዕፎ ለንባብ ያበቃው ‘ያልተሄደበት መንገድ’ የሚለው መፅሀፉ የፖለቲካና የህሊና እስረኛው የመንፈፅ ፅናት ምሥክር ነው። ከሌሎች የፅሁፍ በረከቶቹ በተጨማሪ በ2016 (እአአ) ከቃሊቲ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ፅፎት በሚዲያዎች በወጣው “The Indomitable Spirit” (የማይንበረከከው መንፈስ) በተሰኘው ረዥም የእንግዘሊዝኛ ግጥሙ መኻል የሚከተለውን የፅናትና የተስፋ መልዕክት ያስተውሏል፤ (ትርጉም በዚህ ፅሁፍ አቅራቢ)

መድረሻችን ነፃነት - መሆኑን ላንረሳ
መቆም ለመብታችን - ፍርሃታችንን ላያነሳ
ቼ! ይለናል - የማይንበረከከው መንፈሳችን
እንድንገፋ እንድንቀጥል - ሠላማዊ ፍልሚያችንን!!

የጭቆናው ወጀብ - ቢያላጋ ቢያንገላታን
የአምባገነኖች እሳት - ቢለበልብ ቢፈጀን
የአውሬው መዳፍ - ሊያፍነን ቢጫነን
የምድረበዳው ወላፈን - ደርሶ ቢያንገዳግደን
ግና፤ ይህም ሁሉ ሆኖ
ወደፊት ከመራመድ - ከቶም አንዳች አላገደን።




“መታሰር ምንም ማለት አይደለም። አስሮ ሰብዐዊ መብትን መጣስ ግን የትም ሀገር የሌለ ነው። እንደ ኢትዮጵያ መንግሥት ጨካኝ የለም። 4 በ 5 በሆነች ቤት የምንኖረው 23 ሆነን ነው። እዛችው ቤት ውስጥ ለሽንት የምንጠቀምበት ባልዲና የሁላችንም ልብስ ይቀመጣል። ይህንን ተቃውመን የረሀብ አድማ ብናደርግ ‘ከፈለጋችሁ መሞት ትችላላችሁ’ ነው የተባልነው። እኛም ለመሞት ዝግጁ ነን።” አቶ በቀለ ገርባ 18/03/16 (ምንጭ ሶሻል ሚዲያ) አቶ በቀለ ገርባ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ ምክትል ሊቀ መንበር ሲሆን የሠላማዊ ትግል አራማጅና አንቱ የተባለም ምሁርና ፖለቲከኛም ነው። ከዚህም በተጨማሪ አቶ በቀለ የተለያዩ ፖለቲካ ፓርቲዎች ህብረት የሆነው ‘መድረክ’ (የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ አንድነት መድረክ) የሥራ አስፈፃሚ አባልም ነው። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር ነበረ።

መህይምናኑ ናዚስት ህወሃታውያን ምሁራንን ቱታ በማልበስና በካቴና በማሰር የይስሙላ ፍርድ ቤቶቻቸው እያመላለሱ ለህዝብ በማሳየት የህዝቡን ሥነ ልቡና ለማሚሸሽና ተስፋ ለማስቆረጥ ከመዳከር አልቦዘኑም። በፎቶው ላይ ከፊት የቆመው አቶ በቀለ ገርባ ሲሆን ሌሎቹም በካቴና ታስረው ይታያሉ። አቶ በቀለ ገርባ በትጥቅ ትግል ሥልጣን በመያዝና በሠላማዊ ትግል ሥልጣንን በመረከብ መካከል ያለውን ልዩነት ለከሳሾቹ በካንጋሩው ፍርድ ቤት ሲያስረዳ የሚከተለውን ተናግሯል። “የትጥቅ ትግል በአንድ ወገን ድል አድራጊነት የሚጠናቀቅ እንደመሆኑ አሸናፊውን ወገን ክብርና



የበላይነትን ሲያጐናጽፍ ተሸናፊውን ወገን ደግሞ የውርደትና የበታችነት ስሜት

ይፈጥርበታል። በዚሁ የተነሳ ተሸናፊው ወገን ቂም አርግዞ ጊዜውን ጠብቆ አድፍጦ የሚያደባበት ስለሆነ እውነተኛ ያልሆነ አሉታዊ ሠላም የሰፈነበት ነው። ፖለቲካውም የምሬት፣ የጥላቻ የበቀልና የጠላትነት ስለሚሆን እስራት ስደት ከሥራ መፈናቀልና ሌሎች ምስቅልቅሎችን ያስከትላል። ይህን የትግል ዘዴ በታሪካችን ደጋግመን ሞክረነዋል። መዘዙንም ቀምሰነዋል፤ ለኋላ ቀርነታችን አንደኛው ምክንያት ሆኗልና። በአንፃሩ ግን ሠላማዊ ትግል አሸናፊና ተሸናፊ ስለሌለው መቋጫው እርቅ ወንድማማችነትና ዘላቂ ሰላም ነው። አዎንታዊ ሠላም ፖለቲካውም ልዩነትና ብዙሀንነት ስለሚያስተናግድ የሚማረር ወገን አይኖርም። ስለዚህ ተመራጭ ብቻ ሳይሆን ብቸኛ የትግል ዘዴ መሆን አለበት የሚል እምነት ስላለኝ ህጋዊ በሆነ የፖለቲካ ድርጅት ውስጥ በመሳተፍ የድርሻዬን በማበርከት ላይ እገኛለሁ።



በትጥቅ ትግል ወደ ሥልጣን የሚመጡ መንግስታት ከውይይትና ድርድር ይልቅ በኃይል መፍትሔ ስለሚያምኑ ዴሞክራሲያዊ አካሄድን ከማቀጨጭ አልፎ እስከነአካቴው ይፃረራሉ። ለይስሙላ በሚገኙባቸው የድርድር መድረኮችም ሌላም ወገን እንዲቀበል የሚፈልጉትን ለመንገር እንጂ ሰጥቶ ለመቀበል ስላልሆነ በድርድሩ ማግስት ወደ ቀድሞ የኃይል ተግባራቸው ይመለሳሉ። ህዝቡ የጦር ሜዳ ገድሎቻቸውን አይቶና ሰምቶ አይበገሬነታቸውን ተረድቶ በፍርሃት እንዲገዛላቸው ሚዲያውን በጦርነት ወሬ ያደምቃሉ።

በሰላማዊ ትግል አግባብ ስልጣን የሚይዙት ግን የስልጣናቸው ምንጭ የሆነው ሕዝብ ጥቅሙና መብቱ ካልተጠበቀለት ነገ ደግሞ ለሌላ መስጠት እንደሚችል ስለሚገነዘቡ ዜጎቻቸውን ያከብራሉ፤ ከመፍራት ይልቅ መከበርን ይሻሉ ከመናገር ይልቅ ማዳመጥን ያስቀድማሉ። እውነተኛ ዴሞክራሲን በማስፈን ሕዝባቸውን ወደ ዘላቂ ሰላምና እድገት ይመራሉ። እንደዚህ ዓይነት ሰላማዊ ትግል ነው እንዲካሂድ የምሻውና ዋጋ እየከፈልኩበት ያለሁት” ብሏል።



የአራት ልጆች አባት አቶ በቀለ ገርባ በመሃይምናኑ ናዚስት ህወሃታውያን አስቀድሞ በ2011 (እአአ) ተይዞ በሽብርተኝነት ክስ አራት ዓመታት በወህኒ ከማቀቀ በሁዋላ በ2015 (እአአ) ተለቀቀ። በህዝብ አክብሮትንና ታላቅነትን የተቀበሉ ኢትዮጵያውያን ፖለቲከኞች እንደ ቁልቋል እሾህ የሚኮሰኩሱት ህወሃት አቶ በቀለ ከእስር ተፈትቶ ብዙም ነፃ አየር ሳያገኝና የቤተሰቡን ናፍቆት እንኳን በቅጡ ሳይጠግብ በድጋሚ በሽብርተኝነት ከሶ ከዲሴምበር 2015 (እአአ) ጀምሮ እነሆ ይህ ፅሁፍ እስከተጠናቀረበት 2018 (እአአ) ድረስ በግፈኞች እጅ ወድቆ ይገኛል። የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ አባል የሆኑና ወይም የተጠረጠሩ ከአቶ በቀለ ጋር በናዚስቶች እጅ የሚማቅቁት አያሌ የኦሮሞ ተወላጆች ሲሆኑ ለምሳሌ እነ ደጀኔ ፊጣ ገለታ የኦፌኮ


ፀሀፊ እነ ጉርሜሳ አያኖ እና ሌሎች በሺዎች የሚቆጠሩ እስረኞች በህወሃት አሰቃዮች እጅ ይገኛሉ። (ከላይ የሚታየው ፎቶ፣ Ethiopian security forces roughing up school age kids in Oromia State By Felix Horne)

ወጣት ንግሥት ይርጋ በጎንደር አደባባዮች በሐምሌ ወር 2008 ዓ/ም በተጀመረው



የአማራ ወጣቶች ህዝባዊ የተቃውሞ ማዕበል ውስጥ ለነፃነትና ለፍትህ፣ ለሥርዐት ለውጥና ለህዝብ የበላይነት ድምጿን ከፍ አድራጋ በማሰማቷ በናዚስት ወያኔ ደህንነቶች ደም ለባሽ ዐይን ውስጥ ገባች። እነሆም በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ የአማራ ወጣቶችን በግፍ ያጋዘውና ለኢሰብዐዊ ቶርቸሮች የዳረገው ናዚስት የህወሃት አገዛዝ ንግሥት ይርጋን ከጎንደር አፍኖ በመውሰድ አዲስ አበባ በሚገኘው ማሰቃያው ማዕከላዊ ከተታት። በጎንደርና በባህርዳር በተካሄዱት ህዝባዊ የመብት፣ የነፃነትና የማንነት ጥያቄዎች ከሁለት መቶ ያላነሱ ሠላማዊ ተቃዋሚዎች ሲገደሉ በኦሮሚያ ክልል በተካሄደው አመፅ ደግሞ ቢያንስ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሠላማዊ ተቃዋሚዎች በህወሃት ጥይት መርገፋቸውን የተለያዩ ዓለም ዐቀፍና ሀገራዊ ተቋማት ገልፀዋል።

ወጣት ንግሥት በግፈኛው ህወሃት አገዛዝ የደረሰባትን አካላዊና መንፈሳዊ ቶርቸር




በካንጋሩው ፍርድ ቤት ያቀረበች ሲሆን ‘የኢትዮጵያ ሠብዐዊ መብት ፕሮጀክት’ም በስፋት ዘግቦት ይገኛል። ንግሥት እንዲህ ብላለች “የታሰርኩት በመላው ሀገሪቱ ህዝቦች እየታሰሩና እየተገደሉ መሆኑን በመቃወሜ ነው። በማዕከላዊ ቀዝቃዛና ጨለማ ክፍል ውስጥ ለረዥም ቀናት አስረውኛል። በማታ ለምርመራ በሚል ከታሰርኩበት ክፍል እያወጡ ፖሊሶች ሰብዐዊ ክብሬን የሚያዋርዱ ተግባራትን እየፈፀሙ አሰቃይተውኛል። ወንድ መርማሪዎች እርቃኔን አቁመው ተሳልቀውብኛል። ሴትነቴን እያንቋሸሹ ሰድበውኛል። ሴት ሆኜ መፈጠሬን እንድጠላ የሚያደርጉ ተግባራትን ፈፅመውብኛል። ፀጉሬን በመንቀል ኢሰብዐዊ ድርጊት ፈፅመውብኛል። በማዕከላዊ በየቀኑ ላልተቋረጠ ድብደባ እንግልትና ስቃይ ተዳርጌያለሁ። የእግር ጥፍሮቼን ማዕከላዊ መርማሪዎች ነቃቅለዋቸዋል። ክብሬን



የሚነኩ በማንነቴ ላይ የተመሰረቱ ስድቦችን በፖሊስ መርማሪዎች ተሰድቤያለሁ። የሽብር ክስ ተመስርቶብኝ ቃሊቲ እስር ቤት ከተዘዋወርኩም በሁዋላ የሠብዐዊ መብት ጥሰቱ አልቆመም። እኔን መጠየቅ የሚችሉትንም ስም ዝርዝራቸው በእስር ቤቱ አስተዳደር የታወቁ የቤተሰብ አባላት ብቻ ናቸው። ያም ሆኖ የቤተሰብ አባላትም ቢሆኑ ከምዝገባው ዝርዝር ውስጥ ካልተካተቱ እኔን መጠየቅ አይፈቀድላቸውም። በማንኛውም የሥራ ሰዐት ሳይሆን ከቀኑ ስድስት ሰዐት እስከ ስድስት ሰዐት ተኩል ብቻ ለሰላሳ ደቂቃ ነው የምጠየቀው። ይህ ገደብ እንዲሻሻልልኝ ለፍርድ ቤት በተደጋጋሚ አቤት ብልም ሊቀየርልኝ አልቻለም።

የመብት ጥያቄ ማንሳቴም ለዚህ ሁሉ የሡብዐዊ መብት ጥሰት ሊዳርገኝ አይገባም።” በማለት ድምጿን አሰምታለች፤ ሰሚ መንግሥትና ፈራጅ ዳኛ ባይኖርም።





“ህገ መንግሥቱ የሚለው ይተግበርልን ሥራ ላይ ይዋልልን የሚል ጥያቄ በማንሳታችን ድራማ ሰርተው በቴሌቪዥን ቢያሳዩ የሆነ ነገር ለጣጥፈው ቢሰሩ አስመሳይ የሆኑ ብዙ ነገሮች ቢያደርጉ እኛ የምንገልበት ዓላማ ባይኖረንም የምንሞትለት ዓላማ ግን አለን።” ወጣቱ የሠላማዊ ትግል አራማጅ አህመዲን ጀበል በሺህ ለሚቆጠረው ህዝበ ሙስሊም በአንዋር መስጊድ ካደረገው ንግግረ። ህወሃት የኢትዮጵያን መንበር በተቆጣጠረ ማግሥት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ላይ ዘምቶ ቀብ ባጠለቁ ካድሬዎቹም ቅድስት ቤተ ክርስቲያኗን ተቆጣጥሮ እነሆ በፈጠረው ሡይጣናዊ ምግባር ህዝበ ክርስቲያኑ እስከ ዛሬም ይታመሳል። በተመሳሳይ ምግባሩ ደግሞ ናዚስቱና በቀለኛው ህወሃት ለዘመናት ፀንቶ የቆየውን የኢትዮጵያውያንን ህዝበ ሙስሊም የእምነት ዘርፍ ከሊባኖስ ባስገባው ‘አህባሽ’ ለመተካት በተለይ ከ2011 (እአአ) ባደረገው የሀይማኖት ጣልቃ ገብነት በህዝበ ሙስሊሙ ውስጥ በቀሰቀሰው ሀያል ተቃውሞ ሳቢያ አማኒው ‘የህዝበ ሙስሊሙ የመፍትሂ አፈላላጊ ኮሚቴ’ አቋቁሞ ሠላማዊ ትግሉን ጀመረ። አህመዲን ጀበል የዚህ ኮሚቴ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊ ነበር። ወጣቱ ምሁር በህወሃት ጥርስ ውስጥ ከገባ በሁዋላ ከሌሎች ባልደረቦቹ ጋር በ2012 (እ ኤ አ) ተይዞ በማዕከላዊ በቂሊንጦና ቃሊቲ እስር ቤቶች ውስጥ እጅግ አስከፊ የሆነ በደልና ቶርቸር ተፈፅሞበታል። በ2017 እአአ በወጡ ዘገባዎች በናዚስት አሳሪዎቹ በደረሰበት ሰቆቃ የጤና እክል እንደ ገጠመው ጊዜያዊ ፈውስ ለማግኘት ከታከመበት ቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ከወጡ መረጃዎች ታውቋል። አህመዲን ጀበል በኩላሊትና በሽንት ፊኛ ቱቦ በደረሰበት ጉዳት ለከፋ የጤና አደጋ ቢጋለጥም ናዚስት የህወሃት አገዛዝ በቂ ህክምና እንዲያደርግ ግን አልፈቀደለትም።



የካንጋሩው ህወሃት ፍርድ ቤት በአህመዲን ጀበል ላይ የ22 ዓመት ፅኑ እስራት ፈርዶበታል። አህመዲን ባለፉት አምስት ዓመታት የእስር ቆይታው (እስከ 2010 ዓ/ም) ሶስት ተወዳጅ መፃህፍትን በማዘጋጀት ያቀረበ ወጣት የፍትህና የነፃነት ታጋይ ነው። ናዚስቶችን ካስበረገጋቸው ንግገሩ የሚከተለውን ያስተውሷል። “ዛሬ ሊያስፈራሩን የሞከሩትም ይሁኑ ማንኛውም አካል ህጋዊ ሆነን እስከሄድን ህገ መንግሥታችንን ጠብቀን መብታችን ይከበር በማለታችን ፀረ ሠላም ቢሉን ህገ ወጦች ቢሉን ስም ቢለጥፉልን ሊያስሩን ሊያሸማቅቁን ይችሉ ይሆናል። ሊያስሩን ሊያስፈራሩን ይችሉ ይሆናል። ሊያስሩን ሊደበድቡን ይችሉ ይሆናል። ነገር ግን መቼም ቢሆን የሙስሊሙን ጥያቄ መቀልበስ አይችሉም።” በናዚስት የህወሃት ፍርድ ቤት በካቴና ታስሮ ከሚታየው ከአህመዲን ጀበል ጋር በሽብርተኝነት ከተከሰሱት፤ አቡበከር አህመድ፤ ያሲን ኑሩ እና ካሚል ሽምሱ የ22 ዓመት ፅኑ እስራት የተፈረደባቸው ሲሆን አምስቱ የ18 ዓመት፤ አምስቱ የ15 ዓመት፤ አራቱ ደግሞ የ7 ዓመት ፅኑ እስራት ተፈርዶባቸው ዘመነ ፍዳን እየቆጠሩ ይገኛሉ። ይህንን የግፍ አገዛዝ ዘመን የሚያስር ጊዜ መቸ ይመጣ ይሆን?



“አንተ ባዶ እጅህን መብትህን ለመጠየቅ ስትንቀሳቀስ፣ መሳሪያ ወደታጠቀ አካል በሰላም ስትገሰግስ ባለመሳሪያው ዱላውን ከሰነዘረብህ አሸናፊው አንተ ሰላማዊው ታጋይ ነህ። አሁን ሰላማዊ ትግሉ ፍጹም ሰላማዊነቱን እንደጠበቀ መጠናከር ነው ያለበት። ሰላማዊ ትግል ላይ ልብ ማለት ያለብን ነገር አለ፤ እሱም ሰላማዊ ሆኖ መዝለቅ የሚለው ጉዳይ ነው። ሰላማዊ ታጋይ ይሰደባል፤ ይደበደባል፤ ይሞታልም። ግን ደግሞ ሰላማዊ ታጋይ አይሳደብም፤ አይደባደብም፤ አይገድልም። ይህ ከሆነ ሰላማዊ ትግል ያሸንፋል። አምባገነኖች ሰላማዊ ታጋዮችን በተለያየ መንገድ ከሰላማዊነታቸው እንዲወጡ ሊገፋፏቸው ይሞክራሉ፤ ስሜት ውስጥ በመክተትም የኃይል በትራቸውን ለማሳረፍ ይቋምጣሉ። ይህ ሴራ ሰላማዊ ታጋዮችን ሊያዘናጋቸው አይገባም።” የሠላማዊ ትግል አራማጁ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ። (ፎቶ፤ Eskinder Nega photographed at Addis Court, where he was brought as a witness in a terrorism trial Independent Jan. 6, 2017)




ጋዜጠኛ እና የሰብዐዊ መብት ተሟጋች እንዲሁም የሠላማዊ ትግል አራማጅ ወጣቱና ምሁሩ እስክንድር ነጋ በናዚስቶች ለሰባተኛ ጊዜ የተያዘውና ወህኒ የወረደው በ2012 እአአ ነበር። ናዚስት የህወሃት አገዛዝ በየጊዜው እስክንድርን ቢያስረውምና በፍርሃት ተቃውሞውን ይተዋል እያለ ቢፈታውም እርሱ ህገ ወጦችን በአደባባይ ከመሞገት ከመፃፍና ከመናገር የማይቆጠብ የነፃነት፣ የፍትህና የዴሞክራሲ አቀንቃኝና ታጋይ ስለሆነ በሽብርተኝነትና ህገ መንግሥቱን በሃይል ለመናድ በሚለው ጭምብል ክስ እነሆ የ18 ዓመት ፅኑ እስራት ፈርዶበት በህወሃት ‘ጉላግ’ ከ2012 (እአአ) ጀምሮ የግፍ ዘመንን እየቆጠረ ይገኛል።

ጋዜጠኛ እስክንድር በነፃነት የመፃፍና ሀሳብንም በነፃነት የመግለፅ መብት ይከበርና ይተገበር ዘንድ በርካታ ነፃ ጋዜጦችንና መፅሄቶችን በራሱ ወጪና ኪሳራ ያቋቋመና ያሳተመ ቢሆንም ፀረ ዴሞክራሲው ህወሃት እጅ በእጅ እየተከታተለ ጋዜጦቹንና መፅሄቶቹን ሲዘጋና ‘ህገ ወጥ’ የሚል ታፔላ ሲለጥፍባቸው ኖሯል። ወንጪት፣ አስኳል፣ ምኒልክ እና ሳተናው ጥቂቶቹ ናቸው። እስክንድርና ጋዜጠኛ ባለቤቱ ሰርካለም ፋሲል በግንቦት 1997 ዓ/ም (2005) ተደርጎ የነበረውን ሀገራዊ ምርጫ በጉልበት የቀለበሰውን የህወሃት አገዛዝ ተቃውመው በጋዜጦቻቸው በመፃፋቸው በሽብርተኝነት ተይዘው (ሰርካለም ነፍሰ ጡር ነበረች) በታሰሩበት ወቅት ነበር የመጀመሪያ ልጃቸው ናፍቆት በእስር ቤት የተወለደው። እስክንድር በጋዜጠኝነት ሙያው በሰብዐዊ መብት ታጋይነቱና በህሊና እስረኝነቱ ከተለያዩ ዓለም ዐቀፍ ተቋማት የተለያዩ ሽልማቶች በሌለበት የተበረከተለት ሠላማዊ ታጋይና የተባ ብዕርተኛ ነው። PEN/Barbara Goldsmith Freedom to Write Award, Golden Pen Award of Freedom, World Press



Freedom Hero Award (2017) የተሰኙት ዓለም ዐቀፈ ሽልማቶች ለእስክንድር ከተበረከቱት መኻል ናቸው። (ፎቶ፤ ጋዜጠኛ እስክንድር፤ ባለቤቱ ጋዜጠኛ ሰርካለም ፋሲልና በወህኒ የተወለደው ልጃቸው ናፍቆት እስክንድር - ከሶሻል ሚዲያ)



ጫልቱ ታከለ ትባላለች። የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሁለተኛ ዓመት የሶሲዮሎጂ ተማሪ እንደነበረች በግንቦት 2008 እአአ በዘረኛው የህወሃት አገዛዝ በኦነግ (የኦሮሞ ነፃነት ግንባር) አባልነት ተጠርጥራ ወደ ማዕከላዊ ትጋዛለች። በዚያ የፍዳ አገር ሰቆቃና ቶርቸር ሲፈራረቁባት ቆይታ በካንጋሩው የናዚስቶች ፍርድ ቤት የ12 ዓመት ፅኑ እስራት ተፈርዶባት ወደ ቃሊቲ ሰቆቃ የእስር መንደር ተዘዋወረች። በዚያ የግፍ ሥፍራ ስምንት ዓመት ከአንድ ወር ታስራ በ2016 እአአ ተፈታች። እነሆ ደግሞ ለግፉና ለጭካኔው ለከትና ጣራ የሌለው የናዚስቶች አገዛዝ ከስምንት ዓመት እስር በሁዋላ ለስድስት ወር እንኳን በአንፃራዊ ነፃነት ሳትኖር በማርች 2017 እአአ ከሁለት ጓደኞቿ ጋር አፍኖ ዳግም ወደ ሰቆቃው የእስር መንደር ማዕከላዊ ከትቷታል። በህዳር 28/2010 ዓ/ም በልደታ ምድብ 19ኛ ወንጀል ችሎት (ፍርድ ቤት) የቀረበችው ጫልቱ ታከለ "ከኢህአዴግ ፍርድ ቤት ምንም አንጠብቅም። ወደፊትም ፍትህ እንደማናገኝ ነው የማስበው" ብላ በመናገሯ ጉደኛው ፍርድ ቤት የ500 ብር ቅጣት እንድትከፍል ወስኖባት ቀጣዩን ፍርድ እስኪያሳውቃት ወደ 'መኖሪያዋ' የግፍ ጉረኖ ማዕከላዊ መልሷታል። በናዚስቶች እስር ቤቶች ውስጥ የኦሮሞ ተወላጆች እጅግ ከፍተኛውን ቁጥር በመያዛቸው በእስር ቤቶቹ የመግባቢያ ቋንቋው ኦሮምኛ መሆኑ በይፋ ይነገራል።



ዶ/ር ፍቅሩ ማሩ ሆርዶፋ ይባላሉ። አትዮ ስዊድናዊ የልብ ህክምና ዕውቅ ሰርጀን ናቸው። የዕድሜያቸውን 40 ዓመት የኖሩት በስዊድን ሲሆን በዚሁ ሀገር ስመ ጥር ከተባሉት የልብ ስፔሺያሊስት ዶክተሮች አንዱ ናቸው። እንደውም የሙያቸው ብቃት በመላው አውሮፓ ከሚገኙ ጥቂት ጠበብቶች አንዱ መሆናቸውን ከአውሮፓና ከስዊድን የህክምና ባለሙያዎች የወጡ ጆርናሎችና መረጃዎች ያመለክታሉ። መንፈሳቸው ኢትዮጵያን ያልለቀቀው ዶ/ር ፍቅሩ በሙያቸው ሀገራቸውንና ህዝባቸውን ለማገልገል ወደ ኢትዮጵያ ተጉዘው ሀሳባቸውን በ2007 እአአ ከግብ በማድረስ 'አዲስ የልብ ህክምና ሆስፒታል' በሚል መጠሪያ የተሰየመ አዲስ አበባ ላይ መሰረቱ። እነሆም በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ታላቅ




የሙያው ዝና ያላቸው ዶክተር የልባቸው በመሳካቱ ሆስፒታሉን በማደራጀትና ዘመናዊ በሆኑ የህክምናው ግብዐቶች ወደ ላቀ ደረጃ ለማድረስ አስፈላጊ የሆኑ የህክምና መሳሪያዎችን በቦሌ ሲያስገቡ የህወሃት አገዛዝ በ2010 እአአ "ህገ ወጥ" በሚል ክስ አሰራቸው። ሆኖም ካንጋሩው የህወሃት ፍርድ ቤት "ህገ ወጥ" ያለውን የዕቃ አገባብ ክስ ከአመት በሁዋላ ውድቅ ቢያደርገውምና ዶክተሩን ነፃ ቢላቸውም በ2013 እአአ ዶክተር ፍቅሩ እንደገና ለእስር ተዳረጉ። ሽብርተኝነት የክሱ አንድ አካል ነው። የተማሩና ታላላቅ ኢትዮጵያውያንን በማሳደድ

በመረሸንና በእስር በማሰቃየት የሚታወቀው የበታችነት ስሜት በሽተኛው የናዚስት ህወሃት አገዛዝ ዶ/ር ፍቅሩ ማሩን በሀሰት ወንጀል በግፍ አስሮ ማማቀቁን በመቃወም የስዊድን ጠ/ሚኒስትር ከኢትዮጵያው የህወሃት አፈ ልሳን ጠ/ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝና በጊዜው ከናዚስት ህወሃት ማዕከላዊ ኮሚቴ ከዘጠኙ ፈላጭ ቆራጭ የሥራ አስፈፀሚ አባላት አንዱ ናዚስት እና በወቅቱ የውጪ ጉዳይ ሚ/ር ከነበረው ቴዎድሮስ አድሃኖም ጋር ስብሰባ ተቀምጠው ዶ/ር ፍቅሩን እንዲለቁ ጠይቀዋቸው ነበር። ሆኖም ‘ሳቂታዎቹ ነፍሰ ገዳዮች’ (ዘ ሰማይሊንግ አሳሲንስ) በህይወት ዘመናቸው ፈፅመውት የማያውቁትን ዲያብሎሳዊ ‘ቃል ገብተው’ እነሆ ዶ/ር ፍቅሩን በተጨማሪ ወንጅል ከሰዋቸው አረፉት። በቂሊንጦ እስር ቤት የተነሳውን እሳት ካቀነባበሩት ሽብረተኞች



አንዱ ነህ ብለው ከ 31 ሌሎች እስረኛ ተከሳሾች ጋር እውቁን ካርዲዮሎጂስት በካቴና አስረው የይስሙላ ፍርድ ቤት ያመላልሷቸዋል። ህወሃት በዕውቀት በሰብዕና እና በሀገራዊ ኢትዮጵያዊነት ራዕይ የሚበልጡትን አንቱ የተባሉ ኢትዮጵያውያንን አዲስ አበባን ከተቆጣጠረበት ከ1983 ዓ/ም ማግሥት ጀምሮ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሰበብ ኖረውም አልኖረውም ግማሹን በእሰር ሲያማቅቅ ግማሹን ከሥራ ሲያባርርና ለስደት ሲዳርግ ግማሹንም ሲገድል ኖሯል። በአፍሪካ እና በዓለም የህክምና ጠበብት/ስፔሺያሊስቶች ከፍተኛ እውቅናና ክብር የነበራቸው ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ አልታዬ ናዚስቶች ኢትዮጵያን እንደተቆጣጠሩ በጠሩት ጉባዔ ላይ ‘ሀገርን በጠመንጃ አፈሙዝ ብቻ ያለ ህዝብ ፈቃድና ይሁንታ መገነጣጠል አትችሉም’ በማለታቸው በያዙባቸው ቂም ውለው አድረው በፈጠሩት አስባብ በእስር ቤት አንገላተውና አሰቃይተው ያደረሱባቸው አካላዊና መንፈሰዊ ሰቆቃ በሀገረ አሜሪካ ለህልፈተ ሞት ዳርጓቸዋል። ለሶስት አስርታት በመዝለቅ ላይ የሚገኘው የናዚስት ህወሃት ግፍ ቀለምና ወረቀት የሚበቃው አይመስልም። (ፎቶ፤ ከላይ በስተግራ የሚገኘው የፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ነው - ከዊኪፒዲያ)



Sweden’s prime minister (left), in 2015, speaks with **Dr Tedros Adhanom** (right, middle; then Ethiopia’s foreign minister, now recently elected as WHO Director General) and Ethiopia’s prime minister, **Hailemariam Desalegn** (right, sitting opposite Sweden’s PM). Yet, the unfortunate cardiologist, Dr Fikru Maru, has been given no mercy, as he suffers in one of Ethiopia’s squalid and crowded prisons, where he often has to live in a small room with around 100 other prisoners, often without a mattress to sleep on, and at risk for infectious diseases. (https://drfrankashall.wordpress.com)





ክንድሻቶ ፈረደ ይርጋ ይባላል። አርሶ አደር ነው። የተያዘው ጎንደር ህዳር 9 ቀን 2009 ዓ/ም ከቀን የእርሻ ውሎው ሲመለስ ነው። ‘ሽብርተኝነት’ የመያዙ ሰበብ ነው። ወደ ትግራይ አሻግረውት በገምድ አስረው ጉድጓድ ውስጥ ያለ ምግብና ውሃ አስቀመጡት። ከጉድጓዱ የሰቆቃ ወቅት ቀጥሎ ወደ ሁመራ መልሰውት በሁመራ ወታደራዊ ካምፐ ከፉኛ ድብደባ ፈፀሙበት። በዚህ ድብዳባ ወቅት ነበር ብልቱን የመቱት። በዚህ ህመም ክፉኛ እየተሰቃየ ባህርዳር ቆይቶ ወደ አዲስ አበባ

ቂሊንጦ ወህኒ አመጡት። ለወራት ያለ ህክምና ሲሰቃይ ቆየ። ህመሙ እየፀና በመምጣቱ ቃሊቲ ጤና ጣቢያ፣ ፖሊስ ሆስፒታልና ጥቁር አንበሳ ተመላልሷል። ከብልቱ ሌላ ሆዱ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበት በመሆኑ ቀዶ ጥገና ተደርጎለታል። ፈረደ ሱሪ መልበስ አይችልም። በትክክልም አይራመድም። እንዲህም እየተሰቃየ ናዚስት ህወሃት በወታደር እያጀበ የካንጋሩው ፍርድ ቤት ያመላልሰዋል። በነሚፍታህ ሸህ ሱሩር የክስ መዝገብ ውስጥ 74ኛው ተከሳሽ ነው። ያለ ፍትህ ታስረው ፍትህ በማይገኝበት ፍርድ ቤት እያመላለሱ ስቃያቸውን ለህዝብ ማሳየት በተመልካቹ ሥነ ልቡና ሽብር ለመፍጠር ካልሆነ ምን ሊሆን ይችላል? ከተለያዩ የማዕከላዊ የቂሊንጦ የቃሊቲ የህሊና እስረኞች መረጃ እንደታየው በቶርቸር ወቅት ብዙዎች በብልታቸው ላይ ናዚስት መርማሪዎች በሚያንጠለጥሉባቸው ሁለት ሊትር ውሃ የያዘ ኮዳ ብዙዎች በመኮላሸት ለዕድሜ ልክ የሚዘልቅ ሰቆቃ ተፈፅሞባቸዋል። ይህም በተለያዩ ተጨባጭ የአካል ማስረጃዎች



ተረጋግጧል። (የፈረደን ታሪክ ጋዜጠኛ ጌታቸው ሽፈራው - እራሱም በናዚስቶች እስር ቤት የማቀቀ - ከፍርድ ቤት ውሎ ከዘገበውና በማህበራዊ ሚዲያ ከወጣው በመንቀስ ለዚህ ፅሁፍ በሚስማማ አቀራረብ ተደራጀ)

ዶ/ር መራራ ጉዲና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስ መምህር ነበሩ፣ ፀረ ምሁራኑ ህወሃት ለ35 ዓመት ካስተማሩበት የአ/አ ዩኒቨርሲቲ እስካባረራቸው ድረስ። በኢትዮጵያ ፖለቲካ ተሞክሮ በሳልና አንጋፋ ከሆኑት ጥቂት ኢትዮጵያውያን መኻል አንዱ ናቸው። ዶ/ር መራራ የኦሮሞ ፌዴራሊስት ኮንግረስ (ኦፌኮ) ሊቀ መንበር ናቸው። የሠላመዊ ትግል አራማጅና በሃሳብ ተሸናንፎ ሥልጣንን በህዝብ ድምፅ በዴሞክራሲያዊ መስፈርት በመያዝ የማያወላውል አቋም አላቸው። ህወሃት ኢህአዴግ በሚለው ማዕቀፉ ወደ ሥልጣን ከመጣ ጀምሮ ከፓርላማ እስከ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ድረስ በሚያካሂዷቸው ሀገራዊና ሁለንተናዊ ፖለቲካዊ አመለካከታቸው ከመለስ ዜናዊ እስከ ካድሬዎቹ በጠረጴዛ ዙሪያ ሞግተዋቸዋል፣ መክረዋቸዋል፣ መጪውንም ዘመን



አመላክተዋቸዋል። የሚሰማ ጆሮ የሚያመዛዝን ህሊና የላቸውምና የእኚህን አንጋፋ ምሁርና የፖለቲካ ጠቢብ ተግሳፅም ሆነ ምክር አልሰሙም። አለመስማታቸውም ብቻ ሳይሆን እኚህ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ በተለያዩ መንግሥታትና ድርጅቶችም ከበሬታ ያላቸውን የሠላምና የዴሞክራሲ አራማጅ በ2016 (እአአ) የአውሮፓ ህብረት ፓርላማ ባደረገላቸው ጥሪ ብራስልስ ላይ ተገኝተውና ስለ ኢትዮጵያ የተጠየቁትን አብራርተው አዲስ አበባ ሲመለሱ የህወሃቱ አፈ ልሳን ጠ/ሚኒስትር ሃይለማርያም ደሳለኝ በኦክቶበር 2016 (እአአ) ያወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ድንጋጌ ተላልፈሃል በሚል ዲሴምበር 1/2016 (እአአ) ደህንነቶቹን ልኮ አሰራቸው። የዶክተር መራራ መታሰር 'ያስቆጣቸው' ዓለም ዐቀፍ አካላት ለምሳሌ የአውሮፓ ፓርላማ ፕሬዚዳንት፣ የተወሰኑ የአሜሪካ ሴናተሮች፣ የአውሮፓ ፓርላማ አባላት፣ የአውሮፓ ህብረት የውጪ ግንኙነት ሃላፊ እና ሌሎችም ህወሃት ዶ/ር መራራን እንዲፈታ ጠይቀዋል። ህወሃት የርጥባን ገንዘብ ሲሰጡት እንጂ ደስተኛነቱ እስረኛ ፍታ ሲሉት አይደለምና ጥያቄያቸውን በአንድ ጆሮው ሰምቶ በሌላኛው አፍስሶታል። ያንጋፋው ምሁር መታሰር በተለያዩ ዓለም ዐቀፍ ሚዲያዎችም በሰፊው ተዘግቧል። ለናዚስት ህወሃት ይህ ሁሉ ቁብ አልሰጠውም። እነሆ አንጋፋው የኢትዮጵያ ፖለቲከኛ የሀገር አስታራቂና አድባር በናዚስቶች እስር ቤት በአዛውንት ዘመናቸው እየማቀቁ

ይገኛሉ። ዶ/ር መራራ በተለያዩ ወቅቶች ከፓርላማ ውይይቶች እስከ ኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የምርጫ ክርክሮች አያሌ መሰረታዊ የሆኑ ሀገራዊ ነቁጦችን አንስተው አብራርተዋል፤ የድርጅታቸውንም አቋም ጭምር። (ከታች የሚታየው ፎቶ ናዚስት ህወሃት የህዝቡን ሞራል ለመስበርና ዶ/ር መራራንም ለማሸማቀቅ በካቴና አስሮ ወደ ካንጋሩ ፍርድ ቤት መሳሪያ አስደገኖ ሲወስዳቸው - ከሶሻል ሚዲያ)



“መገንጠል ከኦሮሞ ህዝብ ጥያቄ ጋር አይሄድም፤ የኦሮሞ ህዝብ በስፋቱና በብዛቱ ልክ በኢትዮጵያ ፖለቲካና ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ውስጥ ሁነኛ ስፍራ እንዲኖረው መታገል ነው የሚሻለው። አፄ ኃይለሥላሴ ‘የምንወደውና የሚወደን ህዝባችን’ እያሉ የኢትዮጵያን ዕድገት በ40 ዓመት ወደ ኋላ ጎተቱት። ደርግ ደግሞ ‘አስራ ሰባት የትግልና የድል ዓመታት’ እያለ ኢትዮጵያን ከሶስት ደሀ የዓለም አገሮች አንዷ አደረጋት። ኢህአዴግም በተራው “አንጸባራቂ የልማት ድሎች” እያለን ኢትዮጵያን የዓለም ቁጥር አንድ ደሀ ሀገር አደረጋት። ቢሆንም ኢህአዴግ የወሰደው እርምጃ ደግ ይመስላል። ምክንያቱም “ቀኝ ኋላ ዙር” በተባለ ጊዜ በኢኮኖሚያችን ከዓለም አንደኛ እንሆናለን። ወጣቶቻችን ከዩኒቨርሲቲ ተመርቀው የካቢኔና የካድሬ ወንድምና እህት የደለበ ሥራ ሲያገኙ እነሱ ዲግሪ ይዘው ድንጋይ - ኮብል ስቶን - የሚፈልጡበት ሁኔታ ነው ያለው። ኢትዮጵያ በአፍሪካ አንደኛ የምሁራን ስደት ያለባት ሀገር ናት። ለሀገሪቱ የሚጠቅሙ ብዙ ስራ የሚሰሩ እነዚህ ሰዎች ምን እየሆኑ ነው? ሀገርን ለማልማት የሚችሉ ምሁራን ከመንገድ በተወሰዱ ካድሬዎች ተተክተዋል። ኢህአዴግ ፀረ ምሁራን አቋም እንዳለው ይታወቃል። ኢህአዴግ ምርጥ ህገ መንግሥት አለኝ ይላል። እርግጠኛ ነኝ - ኢህአዴግም ያውቃል - (ተቃዋሚዎች) ከኢህአዴግ የተሻለ ህግ መንግሥት ማውጣት እንደምንችል። የዴሞክራሲ ተቋማት እንዳይወለዱና እንዳያድጉ የሚያደርገው ኢህአዴግ ነው። ማነው የኢትዮጵያን ህዝብ የሚያስለቅሰው? ኢህአዴግ አይደለም እንዴ? “ኢህአዴግ ሁለት ምርኩዞች አሉት። ምርጫ ቦርድና ጠመንጃው። ምርኩዞቹን ያውጣና ያስቀምጥና በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ኢህአዴግን (በምርጫ)



ለማሸነፍ ካልቻልን ኢህአዴግ ለመቶ ዓመት እንዲገዛን እፈርምለታለሁ፤ ዋናው ነገር ምርኩዙን ያውርድ - ብዬ ነበር ከዚህ በፊት። እንግዲህ ኢህአዴግ ምርኩዙንም ሳያስቀምጥ ተወዳድሬ መቶ በመቶ አሸንፌያለሁ ብሏል። እንቆቅልሹ ግን የኢህአዴግ አዲሱ ፓርላማ ስልጣን ይዞ ከአንድ ወር በላይ ሳይቆይ ከየአቅጣጫው ቢያንስ ኦሮሞና አማራ አካባቢ የኢትዮጵያ ህዝብ መቶ በመቶ ተመረጥኩ ባለው ላይ ድንጋይ እየወረወረ መሆኑ ነው።” ዶ/ር መራራ ግልፅና ፊት ለፊት በሆነው አቋማቸው ኢህአዴግ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ የሚፈፅመውን ወደር የለሽ ግፍ አቁሞ ሥልጣኑን በህዝብ ለተመረጠ አካል ቢያስረክብ ውለታ መዋሉ ይሆን ነበር ብለውም ነግረዋቸዋል። የደደቢት ናዚስቶች ግን አልሰሙም ቢሰሙም አልታረሙም እንጂ። ይልቁኑም እኒህን ክቡርና አንጋፋ የኢትዮጵያ አድባር ‘በሽብርተኝነት’ ወንጅለው እነሆ ወህኒ ከተዋቸዋል። (ፎቶ፤ በኦሮሞና በአማራው ክልል ከነበሩ ተቃውሞዎች - ከጉግል ፈልግ ምስሎች)

ወይዘሮ እማዋይሽ ዓለሙ የሶስት ልጆች እናት ናት። ከሚያዚያ 16/2001 ዓ/ም ጀምሮ በናዚስቶች ወህኒ ቤት ትገኛለች። ብርጌዴር ጄኔራል ተፈራ ማሞ፤ ብርጌዴር ጄኔራል

አሳምነው ፅጌ እና ሌሎች በርካታ መኮንኖችንና ሲቪሎችን ጨምሮ ህገ መንግሥቱን




በሃይል ለመናድ የመፈንቅለ መንግሥት ለማድረግ ከግንቦት 7 የፖለቲካ ድርጅት ጋር በማበር በሚል ተይዘው የሽብርተኝነት ክስ ከተመሰረተባቸው መኻል ወ/ሮ እማዋይሽ ዓለሙ አንዷ ናት። እማዋይሽ የባህልና ቱሪዝም መሥሪያ ቤት ባልደረባ ነበረች። እነሆም ካንጋሩው ፍርድ ቤት እማዋይሽን የዕድሜ ልክ እስራት በይኖባት ዘመነ ፍዳን ስትቆጥር ዘጠኝ ዓመት ሆናት - ይህ ፅሁፍ ለንባብ በበቃበት በ2010 ዓ/ም። እማዋይሽ በህወሃት አሪዮሳውያን አሰቃዮች መጠነ ሰፊ ግፍና ቶርቸር ተፈፅሞባታል። ለምርመራ ሲወስዷት ዐይኖቿን ሸፍነውና በካቴና አስረው ሲሆን በምርመራው ክፍል ውስጥ የሚካሄድባት ሰቆቃ መራር ነበር። የእናቷን ሰቃይና ኢፍትሃዊ ፍርድ ስትከታተል ቆይታ በአስገዳጅ ሁኔታዎች ሳቢያ ለስደት የተዳረገችው ልጇ ናርዶስ ዘሪሁን ስለ እናቷ የሚከተውን በሶሻል ሚዲያ ላይ አስፍራለች።

“ፊቱን ባላየውም ደምፁ ይሰማኛል። ዐይኔን በጨርቅ ሸፍኖ ከፍተኛ ድብደባ እያደረሰብኝ ነበር። አንቺ ከዚህ በሠላም አትወጪም። ዕድሜ ልክሽን የሚሰማሽ ህመም ነው ጥዬብሽ እንድትወጪ የማደርገሽ እያለ ከፍተኛ ድብደባ አድርሶብኛል” ከላይ የተፃፈው ታሪክ በዘመነ ህወሃት መሃል ፒያሳ በሚገኘው ፌዴራል ፖሊስ ወንጀል ዘርፍ (ማዕከላዊ) የተፈፀመ ነው። መፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ለማድረግ አሲረሻል ተብላ በመዕከላዊ ሳለች ዘወትር እንዲህ ዐይነት ድብደባዎችን አስተናግዳለች። እነሱ ምርመራ ብለው በሚጠሩት የማሰቃያ ስልታቸው እግሯን ተገልብጣ ተገርፋለች። ጡቶቿን በኤሌክትሪክ ገመድ ተመትታለች። ለረዥም ሠዐታት እንድትቆም ተደርጋለች። ከእነዚህም ሌላ በርካታ ፍዳና መከራ ተቀብላለች። በዚህም አልበቃ ብሎ የዕድሜ ልክ እሰራት ተበይኖባታል። ይህ ሁሉ ግን የእሷን መንፈስ አልሰበረውም። እሷ ዛሬም ስለ ሀገሯ ጉዳይ ትብሰለሰላለች። ትጠይቃለች። ምክንያቱም እሷ መነፈሰ ብርቱዋ እማዋይሽ ዓለሙ ናትና - ብላለች ናርዶስ። ናዚስት ህወሃታውየን ከእናት የተፈጠሩ አይመስሉም። ናዚስት ህወሃታውያን ከአባት የተፈጠሩ አይመስሉም። ናዚስት ህወሃት ከእርሱ ዘር ውጪ ያለው በምድረ ኢትዮጵያ የሚገኘው ሁሉ እንደርሱ የሰው ዘር አይመስለውም። ምክንያቱም ህወሃት ከናዚስት መለስ ዜናዊና ከአያቶቹ የተማረው እርሱ ከትግራዊ ወርቅ ዘር የተገኘ ምርጥ ዘር መሆኑን ብቻ ነውና!! (ናዚስቶች የአርያን ዘር ከዘር ሁሉ የበላይና ምርጥ ነው ይሉ ነበር። ህወሃትን ናዚስት የምንለውም የእነሱ ደቀ መዝሙር በመሆኑና ይህንንም እየተገበረ በመሆኑ ነው።)



ፎቶ፤ የዋልድባ ገዳም ሁለት መነኮሳት ‘በሽብርተኝነት’ ክስ በናዚስቶች ወህኒ ቤት ከሚማቅቁት ማኻል ጥቂቶቹ የሀይማኖት አባቶች ናቸው። ከቀኝ ወደ ግራ ካሉት የዋልድባ ገዳም መነኮሳት የመጀመሪያው መነኩሴ አባ ገብረ ኢየሱስ ይባላሉ። ህዳር 14/2010 ዓ/ም በዋለው ችሎት በእነ አስቻለው ደሴ የሽብርተኝነት የክስ መዝገብ ላይ ከቀረቡት የመጀመሪያው ተከሳሽ አቶ አስቻለው በችሎቱ ውስጥ በአደባባይ ልብሱን በማውለቅ መርማሪዎቹ እንዳኮላሹትና እጅግም መራር ስቃይ እየደረሰበት መሆኑን “የፍትህ ያለህ” በማለት “ለዳኞች” አቤቱታውን አሰምቷል። አቶ አስቻለው አያይዞም ሲናገር

ለህሊናው የከበደውና እጅግም የገረመው ደግሞ የዋልድባውን ገዳም መነኩሴ አባ ገብረ ኢየሱስን በክፉ ሁኔታ ደብድበውና ሰባብረዋቸው እሱ ወደሚገኝበት ጨለማ ክፍል መወርወራቸው መሆኑን ለችሎቱ በይፋ ተናግሯል። ሁለተኛወም መነኩሴ አባ ገብረ ሥላሴ ወልደ ሃይማኖትም በከፋ ሁኔታ ተደብድበው ወደ ጨለማ ቤት መከተታቸው ታውቋል። አባ ገብረ ሥላሴ ለፍርድ ቤቱ እንደተናገሩት የዋልድባ ገዳም አካል የሆነውን ‘አፅመ ቅዱሳን’ን መንግሥት አፈረሰው። በዙሪያው የነበረውንም ደን አወደመው። ድርጊቱን በመቃወም ለሃላፊዎች አቤት አልን። ይኸውና በዚህ ምክንያት ‘ሽብር ፈጣሪዎች’ ተብለን እንሰቃያለን - ብለዋል። በመነኮሳቱ ላይ የሀይማኖት ልብሳችሁን አውልቁ በሚልም ፅኑ ድብደባ እንደተፈፀመባቸውና እኒህን የሀይማኖት አባቶች በከፋ መልኩ ቶርች የሚያደርጋቸው የዞን 5 ሃላፊ በርኸ የተባለ አዛዥ መሆኑንም ጭምር ‘ጆሮ ለሌለው” ፍርድ ቤት ይፋ ተነግሯል። በናዚስት የህወሃት እርኩሳን በኢትዮጵያ ምድር እየተፈፀመ ያለው የግፍ ፅዋ መች ይሆን ሞልቶ የሚያበቃው?! የአባቶችስ ፀሎት ወደ ፈጣሪ የሚደርሰው መቼ ነው?!

እባካችሁ የኢትዮጵያዊነት መሥፈርቶችን አትሸርሽሩ ውብሸት ታዬ (ከዝዋይ ማረሚያ ቤት) በፈሪሃ እግዚአብሔር በኢትዮጵያዊ ሥነ-ምግባር ኮትኩተው ያሳደጉኝን ከመጠን ያለፈ እወዳቸው የነበሩትን አባቴን አጥቼ በዝዋይ ግዞት የጭለማ ክፍል ሀዘን ተቀምጬ እያለሁ አንድ የዋህ ፖሊስ “ሀዘን ለመድረስ አይፈቅዱልህም እንዴ?” በሚል ያቀረበልኝ ጥያቄ ነው። “አልሰሜን…!” አሉ። ምፀቱ ይመርራል፤ይቆጠቁጣል። ኢትዮጵያውያን ወንድሞቼና እህቶቼ! እንደምታስውሱት ሁሉ ዐቃቤ ሕግ የሽብር ማስረጃ ብሎ ያቀረበውና እኔም በችሎቱ ላይ ጉዳዩን ይፋ ያደረኩት የአዛውንቱ



አባቴ ህመም እና ቀዶ ሕክምና ‘Operation’ የሚል ቃል በከሳሾቼ “ጦርነት” ተብሎ መተርጐሙ ብዙዎችን ግራ አጋብቶ ነበር። ምንም ግፉ ቢገፋ ለወንድሜ ኢሜል ያደረግኩት “የአባታችን ኦፕሬሽን በመልካም ሁኔታ ላይ ነው” የሚል ቤተሰባዊ የመረጃ ልውውጥ “የአባታችን ጦርነት እየተካሄደ ነው” ተብሎ በሽብር ማስረጃነት እስከመቅረብ ባልበቃ ነበር። በዚሁ በቅርበት አባቴን እንዳላስታምም “አሸባሪ” ተብዬ እኔም በእስር ተጋዝኩ። ይኸው አባቴም አረፉት። አዛውንት ወላጆቻችንን ማስታመም አልቻልንም። ይህን ማድረግ ሽብርተኝነት ማስረጃ ተደርጐ እስከመመዘዝ የደረሰበት የሞራል ወለል ላይ እየተንከባለልን ነው። በእስር ቤቱ ውስጥ ያሉ ጓደኞቼ እኛ ወዳለንበት የልዩ ቅጣት ክፍል ሀዘን ለመድረስ ጠይቀው ተከለከሉ። ለመሆኑ የት ላይ ነው ያለነው? ወደየት እየተጓዝን ነው? ምንስ ይረባን ይሆን? በግሌ ለኢትዮጵያዊነት መሰረቶች ጥልቅ እምነትም ተስፋም አለኝ። ይህንና ይህን የመሳሰሉትን ልበ ደንዳናነቶች ተፈፀሙና



ባህላችን፤ ወጋችን፤ ግብረገባችን፤ ትውፊቶቻችን አለቀላቸው ማለት አይደለም። በኢትዮጵያዊነት መስፈርቶች እንደ በጋ ጎርፍ ድንገት መጥተው ደግሞ ድንገት የሚሄዱ፤ ተነው የሚቀሩ አይደሉም። እስከዚህ በእርግጠኝነት አውቃለሁ። የማላውቀውና ያልገባኝ የሚጨክኑብንና እንደዚህ አምርረው የጠሉን ወገኖች ይህ “እስከመጨረሻ አጥፋው!” ከቶ ለምን ይሆን? (በስተግራ ያለው ፎቶ - Woubshet Taye’s wife Berhane Tesfaye and their son, Fiteh, accepted the CNN MultiChoice African Journalist Award in 2013, on behalf of the imprisoned journalist.) ከላይ የቀረበው ፅሁፍ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ ከዝዋይ እስር ቤት ፅፎት በአውራምባ ታይምስ ላይ ኤፕሪል 11/2014 እኤአ ከወጣው የተነቀሰ ነው። አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ አዘጋጅ የነበረው

ጋዜጠኛ ውብሸት በ2011 እአአ በናዚስት ህወሃት ተይዞ 'የሽብርተኝነት' ክስ ተመስርቶበት የአስራ አራት ዓመት ፅኑ እስራት ተፈርዶበታል።

ለአምባገነኑ የህወሃት አገዛዝ የይስሙላ ዴሞክራሲ ጥብቅና በመቆም ስለ ተበደሉት ኢትዮጵያውያን የአዞ እንባ ማፍሰስ የማይሰለቻት አሜሪካ ስለ ጋዜጠኛ ውብሸት ታዬ የግፍ እስር የሚከተለውን አስፍራ ነበር። ለነገሩ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄደውን ጅምላ እስር የዘር ፍጅት ኢሰብአዊ ግፍ ቶርቸርና ምድራዊ የህወሃት እርኩሳን ተግባራትን ሁሉ ከነማስረጃዎቹ ጠንቅቃ የምታውቀው አሜሪካ እንደ ህወሃት/ኢህአዴግ ስብሰባ 'መግለጫዎችን' እያወጣች ወንጀሉን/ተግባሩን በቃላት ኳኳታ ከመኮነን ያለፈ የፈየደችው አንዳች ቁብ የለም። እንደውም ብዙ 'ሆያሆዬ' የተጨፈረለት የቀድሞው ፕሬዚዳንቷ ባራክ ኦባማ መቶ በመቶ በፍትሃዊና ሠላማዊ ምርጫ አሸንፌያለሁ ያለውን የህወሃት አገዛዝ አዲስ አበባ ድረስ ተጉዞ 'በዴሞክራሲ የተመረጠ መንግሥት' በማለት 'የሽብር ጦር አጋሩን' ህወሃትን 'ጠበል ረጭቶት' መመለሱን አንዘነጋውም።

U.S. Embassy Zagreb
2 May 2016 ·
Woubishet Taye is an Ethiopian journalist who authorities arrested on June 19, 2011. According to an NGO, he had written a column critical of the ruling party before his arrest. On January 19, 2012, a court in Addis Ababa found him guilty on terrorism-related charges and for receiving payment for terrorist acts. He was subsequently sentenced to 14 years of imprisonment and fines. He is reportedly being held at Ziway prison and has suffered poor health. We encourage the Government of #Ethiopia to release Woubishet Taye, and to ensure that the anti-terrorism law is no longer used to undermine freedom of expression and independent media. #FreethePress - ከጉግል ፈልግ ተገኘ- (የአሜሪካ የዴሞክራሲ ጥብቅና እስከዚህ ድረስ ነው።)



አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ የግንቦት 7 የፖለቲካ ድርጅት ዋና ፀሀፊ ጁላይ 23/2014 (እአአ) በየመን ዋና ከተማ ሰንዓ ዓለም ዐቀፍ አውሮፕላን ጣቢያ ከዱባይ ወደ ኤርትራ ትራንዚት ሲያደርግ ታፈነ። በእንግሊዞች እና ተባባሪዎቻቸው አስተምህሮ የገንዘብና የቁሳቁስ እርዳታ ተጠናክሮ ከደደቢት ጫካ እስከ አዲስ አበባ ምኒልክ ቤተ መንግሥት የዘለቀውና በእነርሱም የስለላ መረብ "የሠየጠነው" እና "የተራቀቀው" የህወሃት ደህንነት አቶ አንዳርጋቸውን ከየመን መንግሥት ጋር አሲሮ ካፈነ በሁዋላ በምሥጢር ወደ ኢትዮጵያ አምጥቶ በማሰር እጅግ በርካታ ፕሮፓጋንዳ ሲረጭ ከርሟል። የእንግሊዝ ዜግነት ያለው አቶ አንዳርጋቸው በህወሃት አገዛዝ ካንጋሩ ፍርድ ቤት በሌለበት ሁለት ጊዜ የሞት ፍርድ የተበየነበት ጠንካራ ስደተኛ ፖለቲከኛ ነው። ህወሃት አቶ አንዳርጋቸውንና ድርጅቱን ግንቦት 7ን በአሸባሪነት የፈረጃቸው ሲሆን ሌሎች በርካቶችን ጨምሮ በሽብርተኝነት በተፈበረከ ክስ በናዚስቶች እጅ ወድቀው የሚማቅቁ ሀገርና ወገን ወዳድ



ኢትዮጵያውያን የድርጅቱ አባላት ይገኛሉ። ናዚስት ህወሃት ዓለም ዐቀፍ ህግን ጥሶና በህገ ወጥ ተባባሪዎቹ ድጋፍ ማፍያዊ አፈና በአቶ አንዳርጋቸው ላይ በውጪ ሀገር በማድረጉ እርኩስ አገዛዙን በሚቃወሙት ላይ ሁሉ የተገኘ ታላቅ ድል አድርጎ ጡሩንባ ሲነፋ ከርሟል - በቴሌቪዥን በሬዲዮ በጋዜጣ በእርሱ በሚመሩት ሶሻል ሚዲያዎች እና በወዘተርፈዎች ሁሉ። ‘እኔን የሚቃወምና ከመንበሬ ለማውረድ የተነሳ የትም ይኑር የት ከመረቤና ከእጄ አያመልጥም - ለዚህም አንዳርጋቸውን ያየ ይመን!’ ይህ ነው የናዚስቱ የህወሃት የስለላው መረብ አዛዥ የርኩሰት ተጋባራት ሁሉ ቁንጮውና ቁልፍ የጌታቸው አሰፋ መልዕክት። (ይናገራል ፎቶ እንዲሉ በቀዳሚው ገፅ በሚታየው ፎቶ ላይ አቶ አንዳርጋቸው ፅጌ በቶርችና ልዩ ልዩ ማሰቃያ ዘዴዎች ክፉኛ ተጎሳቁሎ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ከበስተጀርባው (ባክ ግረውንድ) የቶርች ጬኸት እየተሰማ ስለ ‘አሸባሪ ተጋባራቱ’ ምርመራ አዘል ቃለ ምልልስ ሲሰጥ ነው።) የግንቦት 7 ዋና ፀሀፊ አቶ አንዳርጋቸው በድርጅቱ ፖለቲካዊ ዕምነት ህወሃትን ከኢትዮጵያ ጫንቃ ላይ ማውረድ የሚቻለው ‘በሚገባው ቋንቋ ማናገር’ ሲቻል ነው ከሚል ድምዳሜ ላይ በመድረሱ ከኤርትራ መንግሥት ‘የመነሻ’ መሬት ‘ዕርዳታ’ በማግኘት የድርጅቱን አባላት ወታደራዊ ሥልጠና ኤርትራ ውስጥ በመስጠትና ለፍልሚያ በማዘጋጀት ግንባር ቀደም የድርጅቱ መሪ ነው። ነገር ግን ናዚስት ህወሃት አለመታከት እንደሚደሰኩረው አቶ አንዳርጋቸው ኢትዮጵያን ‘ለማተራመስና ለሻዕቢያ ለማስረከብ’ የሚል ዓለማ አንግቦ አይደለም የሞቀ ትዳሩንና ልጆቹን በሰው ሀገር ጥሎ ህወሃትን ለመፋለም በበርሃ ሲጎሳቆልና በየሀገሩ ሲንከራተት የቆየው። ናዚስቱ ህወሃት ይህንን ሰው በማፈኑ ድርጅቱን ግንቦት 7ንም ያፈነና ያገዛዙን ሌሎች ተቃዋሚዎች ያስደነበረ መስሎት ነበር፤ መሳሳቱንና የመቃብር ጉዞውን ማፋጠኑን የተረዳው ግን ብዙም ሳይቆይ በየአቅጣጫው በተነሳውና ባልበረደው ህዝባዊ ተቃውሞ ነበር። በእንግሊዝ ፓስፖርት ይጓዝ በነበረው አቶ አንዳርጋቸው ላይ የተፈፀመውን ዐለም አቀፋዊ ሽብርተኝነት የእንግሊዝ መንግሥት የተለመደውን ‘አሜሪካዊ መሰል’ መግለጫዊ ተቃውሞ ከማሰማት ባለፈ በዜጋው ላይ ስለ ተፈፀመው የሰብዐዊ መብት ጥሰት የወሰደው ፈርጣማ አቋም ቀርቶ ፈርጣማ ‘ማስፈራሪያ’ እንኳን የለም። አቶ አንዳርጋቸው በናዚስቶች ጉላግ ውስጥ እየተሰቃዩ ካሉት የፖለቲካና የህሊና እስረኞች አንዱ ነው። (በፎቶ የሚታዩት አቶ አንዳርጋቸውና የትዳር አጋሩ ወ/ሮ የምሥራች ከሶስቱ ልጆቻቸው ጋር- ከጉግል ፈልግ)






በናዚስት ህወሃት ወህኒ ቤቶች ውስጥ በመማቀቅ ላይ ከሚገኙት በሺህ ከሚቆጠሩ የህሊና እና የፖለቲካ እስረኞች መኻል ለማሳያነት የቀረቡት የጥቂቶቹ ፎቶዎች። ይህ ፅሁፍ ለንባብ በበቃበት ወቅት ከእኒህ መኻል ጥቂቶቹ ‘ፍርዳቸውን’ ጨርሰውም ሆነ ‘ያለ ፍርድ’ በእስር ቆይተው ወደ ‘ትልቁ እስር ቤት’ የተለቀቁ አሉ። በምትካቸው ደግሞ




ብዙዎች ወደ ሰቆቃው ዓለም የተጋዙ አሉ ይኖራሉም። <u>ናዚስት ህወሃት</u> በኢትዮጵያ መንበር ላይ አዛዥ ናዛዥ ሆኖ እስከቀጠለ ድረስ ከፍፁማዊ ዘረኝነት፣ ከፍፁማዊ አምባገነንነትና ከፍፁማዊ የሀገር ንብረት ዝርፊያ ውጪ ፍትህ ነጻነትና ዴሞክራሲ በምደረ ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያውያን ከቶውንም አይኖሩምና!




(ከግራ ወደ ቀኝ) ጋዜጠኛ አናንያ ሶሪ እና ጋዜጠኛ ኤልያስ ገብሩ በካቴና፣ ለአምስት ዓመታት በናዚስቶች እጅ የማቀቀችው ጋዜጠኛ ርዕዮት ዓለሙ፣ ለአራት ዓመታት በናዚስቶች እጅ የወደቀችው የአንድነት ፓርቲ አባል ቀለብ (አስቴር) ስዩም፣ በናዚስት ህወሃት እጅ የወደቀው የሰማያዊ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ወጣት ምሁርና ፖለቲካኛ ዮናታን ተስፋዬ። (ፎቶዎች ከጉግል ፈልግ ምስሎች)

<u>እንባቢ ሆይ!</u> በኢትዮጵያ ሠማይ ስር በናዚስት ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ /ህወሃት/ አገዛዝ ከ1983 ዓ/ም እስካለንበት 2010 ዓ/ም ያለፍትህ ያለ ወንጀል ያለህግ በመላዋ ኢትዮጵያ ወህኒዎች በግፍ ሠንሰለት ታስረው የሚማቅቁትን የፖለቲካና የህሊና እስረኞች ቁጥርም ሆነ ወይም በየወህኒዎቹ በቶርቸር ማቅቀው ህይወታቸውን ያጡት ምን ያህል እንደሆኑ በትክክል ማወቅ አይቻልም። ይህ ጥንቅር የጥቂቶቹን የሰቆቃ ታሪክ በማንኪያ ጨልፎ በመዘከር ሁለንተናዊ ድባቡን በማጉላት በእስከ አሁኑ የወያኔ አገዛዝ በወህኒዎች የግፍ ፅዋ ተቀበለው ለተፈቱት፣ እንደተቀለፈባቸውም ህይወታቸውን ላጡትና ዛሬም በፍዳ ላይ ለሚገኙት የፖለቲካና የህሊና አስረኞች ሁሉ ማስታወሻ እንዲሆን ታስቦ ተዘጋጀ።

ኢትዮጵያ ሆይ! ልቅሶሽና ፍዳሽ መቼና እንዴት ይሆን የሚያበቃው?

ታህሳስ 2010 ዓ/ም (ጃንዋሪ 2018)
ሲድኒ አውስትራሊያ
mmtessema@gmail.com

<u>ማስታወሻ</u>- ቀጥሎ የቀረበው አስፈንጣሪ (ሊንክ) በናዚስቶች ወህኒ ቤቶች ውስጥ በመማቀቅ ላይ ከሚገኙት የፖለቲካና የህሊና እስረኞች ስማቸውና ማንነታቸው የታወቀውንና የተረጋገጠውን ዝርዝር ነውና ይነበብ ዘንድ በአክብሮት እንጠይቃለን።

http://www.ethioreference.com/archives/9327